ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

በወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የአቋም መግለጫ

ጥር 13፣ 2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ሀገራችን ኢትዮጲያ ያለችበት ፈታኝም ተስፋ ሰጪም ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፤ ማኅበረ- ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ከግምት በማስገባት እና በማጤን የትዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

1. የትግራይ ክልል ህዝቦች፣ በዚህ አንድ ዓመት ብቻ ሳይሆን ላለፉት 47 ዓመታት ለገቡበት እጅግ ፈታኝ ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ቁጠባዊ ፈተና ዋናው ተጠያቂ የህወሓት አመራር ቡድን መሆኑን ትዴፓ በፅናት ያምናል። በህዝቦች መስዋእትነት ከመንበረ-ሥልጣኑ ተባሮ ለ27 ዓመታት ረስቶት በነበረው የትግራይ ህዝብ ጉያ ከተወሸቀበት ግዜ ጀምሮ እንዲሁም ይኸ ቡድን፣ በዚህ አንድ ዓመት ሀገራችን ኢትዮጵያ ያልተፈለገ ጦርነት ውስጥ እንድትገባ በማድረግ፣ የትግራይ፣ የአማራና የአፋር ህዝቦች ላይ በተለይ፣ በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ባጠቃላይ ያደረሰው ከፍተኛና ዘግናኝ ጉዳት በፅኑ እንኮንነዋለን።
2. የትግራይ ክልል ህዝቦች፣ የኢፌዴሪ አንድ አካል፣ የፌደሬሽኑ መስራችና አባል፣ እንዲሁም በሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አመራር ስር ያሉ በመሆናቸው እንደ ሌሎቹ ክልል ህዝቦች በሰላም የመኖር፣ የመልማት፣ የመማር እንዲሁም ከጭቆና ነፃ የመሆን መብቶቻቸው እንዲረጋገጥ ለሚያደርጉት ከባድ ትግል እንዲተባበራቸው እንጠይቃለን።
3. ባሁኑ ሰዓት የትግራይ ክልል ህዝቦች በቃላት መግለፅ በማይቻል እጅግ አስከፊ የህወሓት ስርዓት ጭቆናና አገዛዝ ሥር ይገኛሉ። በተለያየ የማደናገር ቅስቀሳና አሰራሮችን በመጠቀም ወጣቱን ከየቤቱ በማስገደድ እንዲታጠቅ በማድረግ እናቶችና አባቶች ያለ ጧሪ እና ደጋፊ በማስቀረት ተስፋ-ቢስ ክልል አድርገዋታል። በመሆኑም የህወሃት አመራር በትግራይ ክልል ህዝቦች እያደረሰ ያለውን ዘግናኝ ግፍና ጭቆና በፅኑ እየተቃወምን፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ባጠቃላይ የትግራይ ክልል ህዝቦች በተለይ ሠላምና ልማት እንዲረጋገጥ የህወሓት አመራር እና ስርዓቱ ከኢትዮጵያ ምድር መወገድ እንዳለበት ተገንዝቦ ለተግባራዊነቱ ከትዴፓ ጎን መሰለፍ እንደሚኖርበት በፅኑ ያምናል።
4. ህወሓት የሚመራው የትግራይ ክልል ብሄራዊ መንግሥት፣ በህገ-ወጥ እና ኢ-ህገመንግስታዊ «ምርጫ» በማካሄድ ሥልጣን የወጣ ህገ-ወጥ ቡድን መሆኑን የሚታወቅ ሲሆን አሁንም ህወሓት እንደለመደው የፈለፈላቸው «ጫጩች» ፓርቲዎች የትግራይ ክልል ሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም መጠየቃቸውን ከአግርሞት ጋር አጥብቀን እንቃወማለን።
5. ለትግራይ ህዝብ እርዳታ እንዳይደርስ መተላለፊያ መንገዶችን የጦር አውድማ በማድረግ ትራንስፖርት እንዲቋረጥ በመድረግና፣ በብዙ ችግር የገባውንም እርዳታ ለሰራዊቱና ደጋፊዎቹ ብቻ እንዲከፋፈል በማድረግ፣ እንዲሁም የተላኩትን ካሚዮኖችና ነዳጅ ለጦርነት በመጠቀም የትግራይ ህዝብ እንዲቸገር ያደረገው በወሳኝነት የሚጠየቀው ህወሓት ነው። ህወሓት በተመሳሳይ መንገድ የአማራና የዓፋርን ህዝብ እንዲሰደድና ውድመትና ችግር እንዲደርስበት አድርጓል። ካሁን በፊት በትግራይ ክልል ግዜያዊ አስተዳደር በተቋቋመበት ጊዜ፣ የኢፌዴሪ መንግሥት ለትግራይ ክልል ህዝቦች ያሳየው ቀና ወገንተኛነቱ የሚታወስ ሆኖ አሁንም ይኸንን አቋሙን በማደስ በከፍተኛ ችግርና ስቃይ ላሉት ለትግራይ ክልል ህዝቦች እንዲደርስላቸው እንማፀናለን። የመብራት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የትራንስፖርት፣ የአቅርቦት (መድሃኒትና ሌሎችም ጨምሮ) እንዲሁም የእለት ጉርስ እርዳታ ጉዳዮች ላይ የኢፌዴሪ መንግሥት አስቸኳይ ተግባራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ እንጠይቃለን። ለዚህ በከፍተኛ ጭቆናና ስቃይ ውስጥ ላለው ህዝብ ባስቸኳይ ካልተደረሰለት ግን እጅግ አስከፊ ሞትና ጉዳት እንደሚደርስበት እና እንደ ህዝብም ሊያልቅ የሚችልበት አደጋ እንዳንጥበበት ሊታወቅ ይገባል። አሸባሪው የህወሓት ቡድን እርዳታ ለማድረስ በፌደራል መንግስት የተሰማሩትን 1015 (አንድ ሺ አስራ አምስት) ካምዮኖች ይልቀቃቸውና እርዳታው ማቅረቡ ይቀጥሉበት እንላለን፡

6. የኢፌድሪ መንግሥት አለም አቀፋዊ እና ውስጣዊ ጫናዎችን ተቋቁሞ፣ ሀገራችን ከገባችበት ሁለንተናዊ ማነቆ እንድትወጣ እያደረገ ያለውን ጥረት እየደገፍን፣ ሰሞኑ ይሽንን ጥረት ለማሳካት መፈታት የማይገባቸው መላ ኢትዮጵያና በተለይ ትግራይን ጥልቅ መዓት ውስጥ የከተቱ የህወሓት መሰሪ አመራሮችን ጨምሮ ወንጀለኛ እስረኞችን ለፈጸሙት በደል ህዝቡን ይቅርታ እንኳን ሳይጠይቁ መፍታቱ ተገቢ እንዳልሆነ ትዴፓ በአጽኖት ተመልክቶታል።
7. በተጨማሪም የይቅርታና የመቻቻል ምህዳር እንዲሰፍን፣ የምክክር ኮሚሽን መቋቋሙ እየደገፍን ነገር ግን ልክ ካሁን በፊት እንደተቋቋሙትና እስካሁን ፋይዳቸው በወጉ ያልታየው የምክክር መድረኮች እጣ ፈንታ እንዳይገጥመው የመንግሥትና የህዝብ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዳይለየው እያሳሰብንና በሀገራችን ከሚታየው የመካረር፣ ዋልታ-ረገጥነት እና የጦርነት ባህል ወጥተን ወደ ዘላቂ ሠላም፣ ተቋማዊ ዴሞክራሲና ዕድገት እምንሸጋገርበት አዎንታዊ መድረክ በመፍጠር አዲሱ የምክክር ኮሚሽን የራሱን ሚና ያለምንም ተጸእኖ እንዲጫወት እንጠይቃለን።